ነፀነትም የሀልም እንጀራ ሆነው ይቀራሉ። ስለሆነም ታጋይ ሀይሎች በሞላ እነዚህን
ሁለት ጠላቶች ለመደምሰስና ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ለመመስረት መተባበር አለባቸው።

በዚህ አንፃር በእርግጥም የመጀመሪያ እርምጃዎች የተወሰዱና/የኢዴአን መቋቋም
ለምሳሌ/ በመወሰድም ላይ ያሉ ሲሆን ገና ብዙ ትግልና ጥረትን የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኗል።
የወቀተን ተቀዳሚ ተግባርና አቢይ ቅራኔ በመዘንጋት አሁንም በሁለተኛ ደረጃ ልዩነቶችና
ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው የሕብረት ጥረትን ከግራም ከቀኝም የሚያደናቅፉ ዝንባሌ
ዎች ከመከሰት አልተቆጠቡም። ይህም በአፋጣኝና በማያዳግም ሁኔታ ተወግዶ በተባበረ
ክንድ ጠላትን መምታት ያስፈልጋል። ሰፊው ሕዝብ ወሳኝ ነው ብለው የሚያምኑ ኃይሎች
ይህንን እምነታቸውን በተግባር ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ማለት ነው። ከልዩ ልዩ ኃይሉ
ችና ርዕዮተዓለሞች የሚበጀውንና የሚጠቀመውን ሕዝቡ አምኖና በፍቃዱ የሚወስንበት በሕ
ዝብ ምርጫና ድጋፍ የሚቋቋም ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም እንታገላለን እስከልን
ድረስ ገና ጉዞዉ በቅጡ እንኳን ሳይጀምር የእነ ድርጅትና ርዕዮተዓለም የበላይነት
ካልያዘ ለአሷር በሚል መንፈስ ሕብረትን መሸሽ ወይ መቃወም ስህተት ከመሆኑም በላይ
ለሕዝቡ ጠላቶች ጠቢጭ ጥቅምን የሚሰጥ አቀዋም ነው።

የወቅቱ ተቀዳሚ ጥያቄ በርዕዮተዓለም ጥያቄ ላይ መከፋፈል አይደለም። ዘጠኙ
የመከራና የግፍ አገዛዝ አመቶች በአጥፍ ድርብ እንዳይቀጥሉ ከተፈለገ የሕዝቡን ሁለት
ጣምራ ጠላቶች በማጥፋት ተግባር ላይ ተባብሮ መረባረብን የግድ ይላል። እያንዳንዱ
ታጋይ ድርጅትም በመስመሩና በአቋሙ እስከተማመነ ድረስ ወሳኝነትን መራጭነትን ለሰ
ፊው ሕዝብ በመተው ይህንን የሀገሪቷን አቢይ ቅራኔ በመፍታት ተልዕኮ ላይ ከሌሎች ጋር
ተባብሮ መሰማራት ይጠበቅበታል። ኢሕአፓ ሕብረት ሲል የድርጅቶች ነፀነት፣ እኩልነ
ትና እምነት የማይረገጥበትን ሕብረት ነው። ዴሞክራሲን መሠረት ያደረገ ለዴሞክራሲ
የሚታገልን ሕብረት ማለቱ ነው።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጠላቶች የታጠቁ፣ የተደራጁና በሸብርና በጭፍጨፋ የተ
ካኑ ናቸው። የተነጣጠለን የሕዝብ ትግል ተሟሙተውም ሆነ በቀላሉ ለመቀ፣ ሊያዳክሙ
ይችላሉ። ያለፈው ያልተቀነባበረና ያልተባበረ ትግል ይህንን በገሀድ አላሳየምን?
መልሱ ግልፅ ነው። ፋሺስቱ መንግሥት ሀገሪቷን ወደባሰ አዘቅት እየከተታት ከመሄድ
ሌላ የሚያመጣው የለዉም። አጠቃላይ ፋሺስታዊ ቀጥጥሩን አጥብቆ፣ በገጠር የበዝበዛ
ተልዕኮውን በማጧጧፍ ከአርሺ ምርት ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት በከተሞች በሠራተኛው ላይ
ብዝበዛውን አጠናክሮ ኢንዱስትሪ በማስፋፋት ሊደላደልና ሊጠናከር ያቅዳል። ይህ እቅዱ
ከኢምፔሪያሊዝም ጋር መጣበቅን በሀገር ውስጥ ደግሞ አምባገነናዊና ፀረ—ሕዝብ አገዛዙን
መቀጠል የሚጠይቅ ነው። ማለትም ፋሺስቱ መንግሥትና ይህንን መንግሥት በሎሌነት አቀ
ይቶ ኢምፔሪያሊስታዊ ዓላማውን ሊያሟላ የሚጥረው የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ፀረ—ፋሺ
ስት ፀረ—ሶሺል ኢምፔሪያሊስት ታጋይ ሀይሎችን ማዳከምና ማጥፋት ቸሏ የማይሉት ትኩረት
የሚሰጡት ተቀዳሚ የሚሉት ተግባራቸው ነው፣ ይሆናልም።

የሕብረትን አስፈላጊነት ከዚህ አንፃርም መገንዘብ የሚቻል ነው። ሆኖም ተመ
ክሮ እንደሚያሳየው ሕብረት ዴሞክራሲያዊ እምነትንና ፖለቲካዊ ብስለትን ይጠይቃል።
ከጠባብ አስተሳሰብ፣ ከቡድን ወይ ድርጅት ጥቅም ብቻ፣ ከግል ሥልጣን ፍላጎት በመነሳት
"ህብረትን" መሻት ፍሬ—ቢስ ነው። የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም፣ ከራስ መንደር
ብጤረሰብ...ወዘተ ፍላጎት ባሻገር የሀገርን ፍላጎት፣ማስቀደምና ሀቀኛ የሀገር ወዳድ
ነትንና ዴሞክራሲያዊነትን ስሜት ማስፈን ይጠይቃል። ይህ ሲይሆን ቁርቱ እነ ለምራ
አንተ ጥፋ፣ እምነትህንና ሀልዉናህን አጥፋ አለዚያም አጠፋሃለሁ ማለት አልፍም ቃታ

